## በኦሮሞ ህዝብና በሲዳማ ህዝብ መካከል ያለው ታሪካዊ ዝምድናና የመልካም ጉርብትና ግንኙነት በወያኔ መንግስት የትንኮሳ ሴራ ኣይደፈርስም

### የኦሮሞ ነጻነት ግንባርና የሲዳማ ነጻነት ግንባር የጋራ መግለጫ

ከፋፍሎ በመግዛት ፖሊሲው ኣማካኝነት ለዘመናት ስልጣን ላይ መኖርን የሚመኘው የወያኔ መንግስት ለረጅም ዘመናት በሰላም ኣብረው የኖሩ ህዝቦችን ሆን ብሎ ከማጋጨት የተቆጠበበት ወቅት ኣልነበረም። ወደ ስልጣን ከመጣበት ወቅት ኣንስቶ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ብሄርና ብሄረሰቦችን በማጋጨት የሺዎች ህይወት ኣንዲጠፋና በሚሊዮኖች ብር የሚገመት ንብረት እንዲወድም ምክንያት ሆኗል።

የህዝቦች ሰላምና ብልጽግና ፀር የሆነው ይህ ስርኣት እኩይ ተግባሩን በመቀጠል ሰሞኑንም የኦሮሞና የሲዳማ ተጎራባች ነዋሪዎችን ሆን ብሎ ለማጋጨት በስውርም ሆነ በግላጭ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። በዚሁ መሰረት በኣርሲ ዞን ኣጄ ወረዳና በሲዳማ ዞን ሓዋሳ ወረዳ መካከል በምትገኘው ሪማ ዳደሳ በተባለች ቀበሌ ተጎራባች የሆኑትን የኦሮሞና የሲዳማ ተወላጆችን ኣጋጭቷል። ግጭቱ የተከሰተው የወያኔ የጥፋት መልእክተኞች በሁለቱም ወገኖች ውስጥ ተሰግስገው በፈጠሩት ትንኮሳ ሲሆን በግጭቱም በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት መድረሱ ተመዝግቧል።

የወያኔ መንግስት ይህንን ግጭት የጫረበት ዋና ምክንያት ከዚህ ቀደም ይጭራቸው ከነበረው ግጭቶች ምክንያት የተለየ ኣይደለም። ሁል ጊዜ ህዝቦች ጠንካራ የትግል ኣጋርነት ፈጥረው የጋራ ጠላታቸው የሆነውን ስርኣቱን ከመታገል ይልቅ እርስ በራሳቸው ላይ እንዲያነጣጥሩ፣ እርስ በርስ እንዲጠራጠሩ፣ በመካከላቸው በሚጫሩት ግጭቶች ተጠምደው የጋራ ጠላታቸውን እንዲዘነጉ እንዲሁም፣ የጋራ ጠላታቸውን በመታገል ኣላማ ላይ መዋል የነበረበትን ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ በከንቱ ኣባክነው እንዲዳከሙና ለዘላለም በጭቆና ቀንበር ስር ተንበርክከው እንዲኖሩ ለማስገደድ ታስቦ ነው።

በተለይም የወያኔ መንግስት በዚህ ወቅት በኦሮሞና በሲዳማ ህዝቦች መካከል የግጭት ሴራ እየሸረበ ያለው የሲዳማ ህዝብ በሃዋሳ ከተማ ላይ ያለውን የመብት ጥያቄ ዳግም እያሰማ ባለበት ወቅት ነው። የወያኔ ስርኣት ከኣስር ኣመታት በፊትም በኣዋሳ ከተማ ኣቅራቢያ ልዩ ስሟ ሎቄ በተባለች ስፍራ የሃገር ባለቤትነት መብት ጥያቄ ለማሰማት እርጥብ ቅጠል ይዘው ሰላማዊ ሰልፍ በወጡ የሲዳማ ተወላጆች ላይ ተኩስ ከፍቶ ከ100 በላይ ንፁሃን ዜጎችን መግደሉ ኣይዘነጋም።

ትንኮሳን መለያ ባህሪይው ያደረገው ስርኣቱ በኣንድ በኩል የሲዳማን ህዝብ በደቡብ ኣቅጣጫ ጎሮቤቶቹ ከሆኑት ሰላማዊ ህዝቦች ጋር ለማቃቃር ሲል በሃዋሳ ከተማ የባለቤትነት መብት ላይ በኣዲስ መልክ ክርክር ሲያስነሳ በሌላ በኩልም ሲዳማን ታሪካዊ ወዳጅና በኣምቻ ጋብቻ ከተሳሰረው መልካም ጎሮቤቱ ከኦሮሞ ህዝብ ጋር ለማናቆር ያላሰለሰ ጥረት ላይ ይገኛል። ኣሁን በሁለቱ ህዝቦች ተወላጆች መካከል ሪማ ዳደሳ በተባለች ቀበሌ ውስጥ የተሸረበው የግጭት ሴራም የኦሮሞንና የሲዳማን ህዝብ በሁሉም ኣቅጣጫ ኣጣብቂኝ ውስጥ ኣስገብቶ የመብት ትግላቸውን የማሰናከል

ዘመቻ አካል ነው ብለን እናምናለን። ባጭር አገላለጽ በተለያዩ ጊዜያት የኦሮሞን ህዝብ ከአጎራባች ህዝቦች ጋር ለማጋጨት ሲሸረብ የነበረው አይነት ሴራ በሲዳማም ህዝብ ላይ እየተጠነሰሰ ነው ማለት ይቻላል።

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) እና የሲዳማ ነፃነት ግንባር (ሲነግ) የወያኔ መንግስት በተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች በተለይም ደግሞ በኦሮሞና በሲዳማ ህዝቦች መካከል የሚሸርበውን ሴራና በዚሁም ሳቢያ የሚከሰቱትን የግጭት አደጋዎች በጽኑ ያወግዛሉ። የኦሮሞ ህዝብና የሲዳማ ህዝብ የረጅም ዘመን ታሪካዊ ዝምድናና መልካም ጉርብትና እንዳላቸው ይታወቃል። ከዚህም ባሻገር ሁለቱም ህዝቦች ተመሳሳይ የጭቆና ታሪክ ጠባሳ አላቸው። ሁለቱም ባንድ ተመሳሳይ ወቅት በጭቆና ቀንበር ስር እንዲወድቁ ከመገደዳቸውም በላይ እስከ ዛሬም ድረስ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ስልጣን ላይ በተፈራረቁ ገዢዎች እየተገዙ የሚገኙ ናቸው። ስለሆነም እነዚህ ተመሳሳይ የጭቆና አገዛዝ ሰለባ የሆኑ ህዝቦች ጠላት እርስ በርሳቸው ሊያጋጫቸው የሚሸርበውን ማንኛውንም አይነት ሴራ በእንጭጩ ለማክሸፍ አብረው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

ማናቸውም የጭቆና ቀንበር ሰለባ የሆኑ ህዝቦች፣ በተለይም ደግሞ የኦሮሞና የሲዳማ ህዝቦች ጆሮአቸውን ለጠላት ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳ ከማዋስ ተቆጥበው በባህላቸው መሰረት ከሁለቱም ወገኖች የተውጣጡ የሽምግልና ኮሚቴ በማዋቀር በመካከላቸው እርቅ እንዲያወርዱ አስቸኩዋይ ጥሪ እናቀርባለን። አልፎ አልፎ በመካከላቸው ሊከሰት ለሚችለው ማንኛውንም አይነት ማህበራዊ ችግር ከጠላት መንግስት ዘንድ መፍትሄ መጠበቅ ሳይሆን በራሳቸው ባህላዊ ሽምግልና እልባት በማስገኘት የጋራ ሰላም፣ ፍቅርና የመተሳሰብን ባህል በማዳበር እርስ በራሳቸው ሊያባላቸው የሚያልመውን የወያኔ መንግስት እንዲያሳፍሩ የጋራ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። የጋራ ጠላት የሆነውን የወያኔ መንግስት በጋራ ክንድ ድል ማድረግ እንዲቻል ተመሳሳይ የጭቆና ገፈት ቀማሽ የሆኑ ህዝቦች የሚፈጥሩት የትግል ትብብር ወሳኝ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ማሳሰብ እንወዳለን።

የተጨቆኑ ህዝቦች ትግል ያሸንፋል!!

የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)

የሲዳማ ነፃነት ግንባር (ሲነግ)

ሰኔ 29, 2012